

koudijs

powered by royal de heus

AKF

# የተመጣጠነ መኖ ለተሻለ ምርታማነት

አለማ ካውዲያስ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፋብሪካ  በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ የሆነ የመኖ ማምረቻ ሲሆን ፤ ይህ ድርጅት ዴሁስ (DE HEUS) ከተባለ አለማቀፍ የእንስሳት መኖ ድርጅት ጋር በጋራ የሚሰራ ድርጅት ነው፤

ዴሁስ( DE HEUS) የእንስሳት መኖ ድርጅት የተመሰረተው በሆላንድ ሀገር ሲሆን ባለፍት 100 አመታት በእንስሳት መኖ ላይ ሲሰራ ቆይቶል፤ይህ ድርጅት በመላው አለም የራሱ የሆነ መኖ ማምረቻዎች ያሉት አለማቀፍ የመኖ ማምረቻ ድርጅት ነው፤አለማ ካውዲያስ መኖ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ፋብሪካ ከዚህ ዴሁስ( DE HEUS) ከተባለ አለማቀፍ የመኖ ማምረቻ ጋር በጋራ በመስራቱ ዴሁስ( DE HEUS) ባለፉት 100 ዓመታት ካገኛቸው ልምዶችና ዕውቀቶች መጠቀም ችሏል፤

### የወተት ላም መኖ አይነቶች፤

- የጥጃ ማሳደግያ ፔሌት መኖ
- የጊደር መኖ
- የወተት ላም ቤዚክ መኖ
- የወተት ላም ኤክሰለንት መኖ
- የወተት ላም ሱፐር መኖ

### የጥጃ ማሳደግያ ፔሌት መኖ

ጥጆች ልክ እንደ ህጻን ልጆቻችን ናቸው፤ ስለዚህም የተለየ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል፤ጥጆች ጥሩ ምርት የሚሰጡ የወተት ላሞች እንዲሆኑ እጅግ በጣም ጥሩ የሆነና የተመጣጠነ መኖ ልንመግባቸው ይገባል፤በዚህ ረገድ አለማ ካውዲያስ የእንስሳት መኖ ማምረቻ ፋብሪካ የተለየ የጥጃ ማሳደግያ ፔሌታይዝድ መኖ ያቀርባል፤ ይህ የመኖ አይነት በውስጡ ለጥጃው እድገትና ምርታማነት ጠቃሚ የሆኑ ከፍተኛ የሆነ ሀይል ሰጪ፣ፕሮቲን፣ቫይታሚንና ማዕድናት ይዟል፤

| ጥጆች ከተወለዱ በሆዋላ | መኖ |
|---|---|
| ከ 1 እስከ 3 ተኛው ቀን | በቂ እንገር መስጠት |
| ከ 1 እስከ 3 ተኛው ሳምንት | ወተትና ውሀ |
| ከ 4 እስከ 10 ኛው ሳምንት | ወተት፡ ውሀ ፡የሳር ድርቆሽና የጥጃ ፔሌት  መኖ መስጠት |
| እስከ 6 ተኛው ወር ድረስ | ውሀ፡ የሳር ድርቆሽና እስከ 3 ኪ .ግ የጥጃ መኖ መስጠት |

### የጊደር መኖ

የጥጃ ማሳደግያ ፔሌታይዝድ መኖ ከተጠቀምን በሆዋላ አድሚያቸው ሲደርስ ወደ ጊደር መኖ መለወጥ ይኖርብናል፤ጊደሮች በልጅነት እድገት ውስጥ ስላሉ ከ ድርቆሽ ሳር ሌላ የተመጣጠነ የጊደር መኖ ያስፈልጋቸዋል፤ የጊደር መኖ ከጥጃነት ወደ ወትተ ላምነት ለሚደረግ የእድገት ሽግግር በጣም ጠቃሚ የሆነ የመኖ አይነት ነው፤ ከ 8ተኛው ወር እስከ 15ተኛው ወር ባለው እድሚያቸው ጊዜ ውስጥ በምናቀርብላቸው ድርቆሽ ጥራትና የሰውነት አቆማችው ላይ በመመስረት ከ 2 እስከ 3 ኪሎግራም የጊደር መኖ መመገብ ይኖርባቸዋል፤

## የወተት ላም ቤዚክ መኖ

ይህ መኖ ለአገር ውስጥ ዝርያ ላላቸውና የውጪ የደም ዝርያ መጠናቸው አነስተኛ ለሆኑ ዲቃላ ላሞች ተስማሚ የሆነ የመኖ አይነት ነው፤ ግባችን ተመጣጣኝ የሆነ ምርት ለማግኘት ከሆነ ይህ መኖ ጥሩና ተመራጭ አይነት ነው፤ የወተት ላም ቤዚክ መኖ በውስጡ አስፈላጊውን ንጥረ ምግብ ሁሉ የያዘ ሆኖ ከወተት ላም እርባታ የሚጠበቀውን ውጤት ሊያስገኝ የሚያስችል የመኖ አይነት ነው፤

## የወተት ላም ኤክሰለንት መኖ

ከፍተኛ የውጪ የደም ዝርያ ያላቸውን የተዳቀሉ የወተት ላም ለሚያረቡ እና ከእርባታውም ከፍተኛ የሆነ ምርት እና ትርፍ ለሚፈልጉ የወተት ላም አርቢዎች ይህ የወተት ላም ኤክሰለንት መኖ ተመራጭ የመኖ አይነት ነው፤ ይህ የመኖ አይነት በእርባታችን ውስጥ ካለው ድርቆሽ ጋር በተመጣጠነ መልኩ ከፍተኛ የሆነ የፕሮቲን፣የኃይል ሰጪ፣የቫይታሚን እና የተለያዩ ንጥረ ምግቦችን በውስጡ የያዘ ነው፤የወተት ላም ኤክሰለንት መኖ በውስጡ ከፍተኛ የቫይታሚን መጠን በውስጡ ስላለ የወተት ላሞች በቀላሉ እርግዝና እንዲይዙ እና ጤናማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤

## የወተት ላም ሱፐር መኖ

ይህ መኖ የምርጦች ሁሉ ምርጥ የመኖ አይነት ነው፤የወተት ላም ሱፐር መኖ ከፍተኛ የሆነ ምርታማነትን፣ጤንነትን እና ትርፋማነትን ትኩረት አድርገው ለሚሰሩ የወተት ላም አርቢዎች ተመራጭ የሆነ  የመኖ አይነት ነው፤ በውስጡ ከፍተኛ መጠን ያለው ንጥረ ምግብ የያዘ ሲሆን ከፍተኛ የሆነ ምርታማነትን፣የመራባት አቅምን እና ጤንነትን ሊሰጥ የሚችል የመኖ አይነት ነው፤

## የወተት ላሞች በማይታለቡበት ወቅት

በዚህ ወቅት የወተት ላሞችን የሰውነት አቆሟቸውን በማየት ልንመግባቸው ይገባል፤ የሰውነት አቋሟቸው  ጥሩ ከሆኑ የተመጣጠነ የወተት ላም መኖ አያስፈልጋቸውም፤ነገር ግን የሰውነት አቋሟቸው ከሚጠበቀው በታች በሚሆኑበት ጊዜ እንደምርጫችን የወተት ላም መኖ መስጠት ይኖርብናል፤ የተመጣጠነ የወተት ላም መኖ ላሞች ከመውለዳቸው ከ 1 ሳምንት በፊት አስቀድሞ መመገብ መጀመር፤ ቀስ በቀስ የመኖ መጠኑን በመጨመር (በሚሰጡት የወተት ምርት መሰረት በማድረግ) በሚወልዱበት ጊዜ እስከ 5 ኪ.ግ ድረስ በቀን መመገብ ይኖርብናል፤

## የአለማ ካውዲያስን የወተት ላም መኖን መቼ እና እንዴት መጠቀም አለብን;

ለወተት ላሞች የምንሰጠው የመኖ መጠን በሚሰጡት የወተት ምርት መጠን የሚወሰን ሲሆን፤ ከፍተኛ የወተት ምርት ለሚሰጡ የወተት ላሞች በመጀመሪያዎቹ የወተት ምርት ጊዜያት ውስጥ ዝቅተኛ የወተት ምርት ከሚሰጡ የወተት ላሞች ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የመኖ መጠን ያስፈልጋቸዋል፤

## ከዚህ በታች  መኖውን እንዴት መጠቀም እንዳለባችሁ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የወተት ምርት በሊትር | የተመጣጠነ የወተት ላም መኖ በኪሎግራም  በቀን |
|---|---|
| 30 | 12 |
| 28 | 12 |
| 26 | 12 |
| 24 | 12 |
| 22 | 11 |
| 20 | 10 |
| 18 | 9 |
| 16 | 8 |
| 14 | 7 |
| 12 | 6 |
| 10 | 5 |
| 8 | 4 |
| 6 | 3 |
| 4 | 2 |

## ለወተት ላሞች  መሰረታዊ የስኬት መርሆዎች

- ድርቆሽ፡ ሁልግዜ ድርቆሽ በመመገቢያ ቦታ ላይ መኖሩን እርግጠኛ መሆን አለብን፡- 24 ሰዓት በቀን፣7 ቀናት በሳምንት፤
- ውሀ፡ውሀ በቀላሉ የምናገኘው ነገር ቢሆንም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ሁልግዜ ላሞቻችን ውሀ ማግኘታቸውን አርግጠኛ መሆን አለብን፤
- በደረቁ መመገብ፡አስፈላጊውን ውጤት ለማግኘት የአለማ ካውዲያስን የወተት ላም መኖ ደረቁን መመገብ ይኖርብናል፤መኖውን ከውሀ ጋር መቀየጥ የለብንም፤

**ALEMA KOUDIJS FEED PLC**
Ziquala Road, PO BOX  Debre Zeit, Ethiopia tel. 011 433 0662, 011652 5592
sales.akf@gmail.com, alemakoudijs@gmail.com

08.1/2015/KR